# <u>አሜሪካ፤ የራሷ እያረረባት የሰው ባታማስልስ?</u>

## ስለሞን ሽፈራው

09-08-17

በተለይም የቀድሞዋ ሶቬት ህብረት መፈራረሷን ተከትሎ የምድራችን ብቸኛዋ ልዕለ ሃያል አገር ተደርጋ መቆጠር የጀመረችው ዩ.ኤስ. አሜሪካ፤ ረጃጅም እጆቿን የማታስገባበት ዓለም አቀፍ ርዕሰ ጉዳይ የለም ማለት ይቻላል። ለዚህ እንደዋነኛ ምክንያት የሚወሰደውም ደግሞ ያቺ አገር በምጣኔ ሀብታዊ እድገቷ የዘመናችን ዓለም ቁንጮ ለመሆን የበቃችበትን ክፍታ መቆናጠጧ ነው። እናም "ያለው ማማሩ ያጣ መደበሩ" እንዲል ያገሬ ወጣት፤ ባለፀጋዋ አሜሪካ፤ ፈጽሞ በማይመለከታት የሌሎች ሉዓላዊ ሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጥልቅ እያለች፤ መንግስትን አስወግዳ ለእርሷ ትዕዛዝ በሚገዛ ሌላ መንግስት እስከመተካት የምትደርስበት አግባብ ስለመኖሩ የሚያከራክር አይሆንም።

ይሁን እንጂ ግን ይህን የአሜሪካ ማን አለብኝነት አሜን ብለው ለመቀበል የማይፈቅዱና የራሳቸውን ሀገር ውስጣዊ ጉዳይ በሚመለከት ከአሜሪካ ፖለቲካዊ እጅ ጥምዘዛ በፀዳ መልኩ ለመጨረስ ከመፈለግ የሚመነጭ የነፃነት ጥያቄ የሚያነሱ መንግስታት ጥቂት እንዳልሆኑም ደፍሮ መናገር ይቻላል። በድህረ ቀዝቃዛው ጦርነት ዓለም አቀፋዊ የፖለቲካ ኢኮኖሚ እውነታ ውስጥ፤ ልዕለ ሃያሏ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ረጃጅም እጆቿን እንዳሻት ጣልቃ እያስገባች በራሷ አምሳል ልትቀርጸው ስትሞክር ያልተስተዋለችበት አንድም አንኳን የሉዓላዊ ሀገር መንግስት ሊኖር እንደማይችል አስረግጠው የሚያስረዱ ተንታኞች መበራከታቸውም ያለምክንያት አይደለም። ይልቅስ የኋይት ሀውስ መንግስታት ነገረ ስራ ሁሉ "ከወፈሩ ሰው አይፈሩ" የሚያሰኝና ፍትሐዊ የፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ስልጣን ክፍፍልን ገድሎ ለመቅበር የሚቃጣው እየሆነ የሚገኝበት አጋጣሚ ጥቂት ስላይደለ እንጂ።

እናም የዓለማችንን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ በብቸኝነት ተቆጣጥራ ሌሎች ሀገራት ሁሉ ለርሷ ብሔራዊ ጥቅም መረጋገጥ የሚስማማ መንግስታዊ የአስተዳደር ዘይቤ እንዲከተሉ ለማድረግ ያለመ ፈርጀ ብዙ ተጽዕኖዋን ለማሳደር የምትሞክርበትን ጣልቃ ገብነት፤ በፀጋ ያለመቀበል አዝማሚያ የሚያሳዩ ነፃ መንግስታት ላይ ጥርሷን ከመንከስ ቦዝና እንደማታውቅ ተደጋግሞ የሚነገርላት አሜሪካ፤ ከዘመነ ኢ.ህአዴግ ኢትዮጵያ አጠቃላይ የስር ነቀል ለውጥ ሂደት በስተጀርባ ለሚዶለት የቅልበሳ ሴራ ድጋፍ የምትሰጥበት አግባብ መኖሩ የሚያከራክር ጉዳይ አይደለም። ለዚህም ደግሞ በድህረ ቀዝቃዛው ጦርነት የአሜሪካ ፖለቲካዊ ታሪክ ውስጥ፤ ዴሞክራትንም ሆነ የሪፐብሊካኑን ፓርቲ ወክለው በህዝብ እየተመረጡ ወደ ኋይት ሐውስ የመግባት ዕድል የገጠማቸው የአሜሪካ ፕሬዚዳንቶች በሙሉ፤ የየራሳቸውን ግልጽና ግልጽ ያልሆነ ጣልቃ ገብነት ተጠቅመው፤ ኢህአዴግ መራሹን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ መንግስት የማንበርከክና የዚችን ሀገር የውስጥ ጉዳይ ለእነርሱ ገደብ የለሽ ፍላጎት መሳካት እንዲያመች አርገው ለመቅረጽም ጭምር ሲሞክሩ ያልተስተዋሉበት አጋጣሚ እንዳልነበር፤ ተጨባጭ አብነቶችን እያነሳን በመነጋገር መተማመን የምንችል ሆኖ ይሰማኛል።

ከዚህ አኳያ የተሻለ ምሳሌ ተደርጎ ሊጠቀስ ይችላል የምለውም፤ በተለይ እንደነ “ሒውማን ራይትስወች” እንዲሁም ደግሞ “አምኒስቲ ኢንተርናሽናል” እና “ሲ.ፒ.ጄ”ን የመሳሰሉት ምዕራባውያን የ“ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት ተቆርቋሪ ነን” ባይ ዓለም አቀፍ ተቋማት፤ ኢህአዴግ መራሹ መንግስት ወደ ስልጣን ከመጣ ጀምሮ መሰረተ ቢስ ወንጀላቸውን እየፈበረኩ በማናፈስ መጠመዳቸው ነው። ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ሀገራችን ለተያያዘችው ስርነቀል የለውጥ ሂደት በጎ ገጽታ ተገቢ እውቅና እንዳይሰጥ ሲሉ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም ብለን እውነታውን በተሻለ መልኩ የሚገልፀው ይመስለኛል። በግልጽ አነጋገር፤ ተጠቃሾቹ በስመ “ለሰብዓዊና ለዴሞክራሲያዊ መብት መቆርቆር” ሽፋን ዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉ የሚነገርላቸው ኒዮ ሊበራሊስት ቡድኖች፤ የኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎችም በውስጣዊ ጉዳያቸው ጣልቃ ለሚገቡ የውጪ ኃይሎች እጅ ያለመስጠት አዝማሚያ በማሳየት የሚታወቁ የታዳጊ ሀገራት ጠንካራ መንግስታትን ግንባር ቀደም የበሬ ወለደ ውንጀላቸው ኢላማ የሚያደርጉበት ፖለቲካዊ ሴራ፤ አሜሪካ ሰራሽ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል የሚል አቋም የሚያራምዱ ተንታኞች ጥቂት አይደሉም።

ደግነቱ ግን፤ ለወትሮው የመላው ሰብዓዊ ፍጡር መብትና ነፃነት ዋስ ጠበቃ፤ ወይም ደግሞ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ቁንጮ ተደርጋ ትቆጠር የነበረችው የዓለማችን ልዕለ ሃያሏ ሀገር አሜሪካ ጭምር፤ በራሷው ዜጎች መካከል ተደጋግሞ በሚከሰት የእርስ በርስ ቅራኔና ግጭት ምክንያት ውስጣዊ ሰላሟ ክፉኛ እየተፈተነ ስለመሆኑ ድፍን የዓለማችን ማህበረሰብ አውርቶ የጨረሰው ጉልህ እውነታ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህ አስተያየቴ ተጨባጭ ማሳያ ማቅረብ ካለብኝም ደግሞ፤ ምናልባትም ከዛሬዋ ኢትዮጵያ ይልቅ የዛሬዋ አሜሪካ ውስጥ ሰላማዊ ሰዎች ቀንተቀን በግፍ ሲገደሉ የሚስተዋልበት የሰላምና መረጋጋት ችግር ስለመኖሩ የሚያመለክቱ ዓለም አቀፋዊ መረጃዎችን በዋቢነት ማንሳት አያዳግትም።

ለአብነት ያህልም፤ ቁጥራቸው የበዛ የሪፐብሊካን ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች መጠነ ሰፊ ትርፍ እንደሚያጋብሱበት የሚነገርለትን ሕጋዊ የጦር መሳሪያ ንግድ በአግባቡ ለመቆጣጠር ካለመቻሉ የተነሳ፤ ራሳቸው አሜሪካውያን ዜጎች ሰላማዊ ህዝብ ተሰባስቦ በሚገኝባቸው ስፍራዎች ላይ የተኩስ እሩምታ እየተከፈቱ ከሚያደርሱት ጉዳት ጋር በተያያዘ ብቻ፤ በዓመት ውስጥ ከሁለት ሺህ የማያንሱ ንፁሃን ሰዎች ይገደላሉ። ይህ ሁኔታ ሲደጋገም የሚስተዋልበት አሰቃቂ ትዕይንት ለኋይት ሀውስ መንግስት ተወራራሽ ራስ ምታት ሆኖ ከቀጠለ ዓመታትን የማስቆጠሩ ጉዳይም የሚካድ አይደለም። ከዚህ የተነሳም የችግሩን ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ እየተባባሰ መምጣት የማይክደው የልዕለ ሀያሏ ሀገር መንግስት፤ ለድንገተኛ የአውቶማቲክ ጦር መሳሪያ የተኩስ እሩምታ አደጋ ትርጉም ያለው ዘላቂ መፍትሔ ሊያገኝለት ባለመቻሉ ምክንያት፤ የዛሬዋ አሜሪካ አብዛኛው ሰላማዊ ዜጋ እንደወጣሁ እቀር ይሆን? ከሚል ብርቱ የደህንነት ስጋት ጋር የእለት ተእለት ህይወቱን ይገፋ ዘንድ አድርጎታል ነው የሚባለው።

ይህ ለፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ የስምንት ዓመታት ስኬታማ አመራር ሳይቀር በቀላሉ የማይሞከር ጉዳይ ሆኖ እንደቆየ የሚታወቅ የጦር መሳሪያ ንግድን በአግባቡ መቆጣጠር ካለመቻል የሚነጭ የሰላማዊ አሜሪካውያን ዜጎች ብርቱ የደህንነት ስጋት መፍትሔ ሳይገኝለት የኋይት ሐውስ አስተዳደር፤ ለመላው የዓለም ህዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት መከበር ዋስ ጠበቃ ሆኖ ሊቆም ሲቃጣው መስተዋሉ በየትኛው የሞራል ብቃት ነው? ሲሉ የሚጠይቁ ታዛቢዎች መበራከታቸውም ታመናልና። ይሁን እንጂ፤

እንኳንስ ከላይ በተመለከተው መልኩ የሚፈፀም የነፍስ ግድያ ወንጀል ምክንያት ብዙ ሺህ ንፁሃን አሜሪካውያን ዜጎች ድንገት እንደወጡ የቀሩበትን አሳሳቢ የደህንነት ችግር ትርጉም ባለው መልኩ ሊፈቱት ቀርቶ፤ የነጮችን የበላይነት ለመመለስ በሚሹ አክራሪዎችና በጥቁሮቹ አሜሪካውያን መካከል የሚስተዋለው ፍጥጫ ወደ ለየለት የጠላትነት ትርምስ እንዲያመሩ ሳያደርጋቸው እንዳልቀረ ነው ሰሞነኛ ዘገባዎች የሚጠቁሙበት።

ይልቁንም ደግሞ አወዛጋቢው የልዕለ ሃያሏ ሀገር አርባ አምስተኛ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ፤ የነጭ አክራሪነት የተጠናወታቸውን ጽንፈኞች በቅጡ የማውገዝ ድፍረት አንሷቸው ተስተውለዋል ከሚል ቁጣ በመነጨ የጥቁር አሜሪካውያን መሬት እንቀጥቅጥ ተቃውሞ ምክንያት፤ ለገላጋይ ያስቸገረ ጎራ ለይቶ የመገዳደል አደጋ በተከሰተባቸው አንዳንድ የዚያች አገር ግዛቶች፤ የፌደራሉ መንግስት መደበኛ ጦር ሰራዊት ጣልቃ እስከ መግባት የደረሰበት ሁኔታ መኖሩን ነው ምንጮች የሚያመለክቱት። እንግዲያውስ ከሞላ ጎደል ይህን በሚመስል አሳሳቢ የሰላምና መረጋጋት ችግር ምክንያት ዜጎቿ እርስ በርሳቸው እየተገዳደሉ በሚገኙበት ብሔራዊ የደህንነት ቀውስ አዙሪት ውስጥ ስለመግባቷ ጉዳይ መላው የዓለማችን ማህበረሰብ የተናገረላት አሜሪካ ናት የዛሬዋ ኢትዮጵያ “አደገኛ የፀጥታ ስጋት ያለባት ሀገር” እንደሆነች አድርጋ ለማቅረብ ሲቃጣት የምትደመጠውም።

ለምሳሌ ያህልም፤ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ከጥቂት ሳምንታት በፊት ባወጣው ወቅታዊ መግለጫ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ አሜሪካውያን ዜጎች “ከአዲስ አበባ ወደ ጅግጅጋና ሐረር በሚወስደው መስመር ላይ ጦርነት መቀስቀሱን የሚያመለክት መረጃ ስለደረሰኝ ወደዚያ አቅጣጫ እንዳትሔዱ” ሲል አስጠንቅቆ እንደነበር አይዘነጋም። የያኔው የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መግለጫ ላይ የተላለፈው ማስጠንቀቂያ ምንም ዓይነት ምንጭ ያልተጠቀሰበትና መሰረተ ቢስ ወሬ ስለመሆኑ በወቅቱ የኢፌድሪ መንግስት የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ ሚኒስቴር ዶክተር ነገሪ ሌንጮ ለመገናኛ ብዙኃን በሰጡት ማስተባበያ አስረግጠው መናገራቸውንም አስታውሳለሁ። ይሁን እንጂ የኋይት ሀውስ አስተዳደር አሁንም ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የሰላምና መረጋጋት አለመኖር ጉዳይ፤ ከኢፌዴሪ መንግስት ባለድርሻ አካላት የተሻለ መረጃ የሚያገኝ የሚያስመስልበትን “ማስጠንቀቂያ” ለዜጎቹ ማስተላለፉን ቀጥሏል።

እኔን ይበልጥ ያስገረመኝ ነገር ደግሞ የፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ መንግስት እዚህ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ አሜሪካውያን ወደ ባህርና ወደ ጎንደርም ጭምር እንዳይጓዙ የሚያስጠነቅቅ መግለጫ በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴሩ በኩል ማውጣቱ ነው። ታዲያ ይሄ የትራምፕ አሜሪካ ዲፕሎማሲያዊ ድንበር ዘለልነት “የራሷ እያረረባት የሰው ድስት ታማስላለች” የሚለውን የአማርኛ ጎምቱ ተረት አያስታውስንም ወገኖቼ!? ለማንኛውም ግን ልዕለ ሃያሏ ሀገር አሁን ላይ ስለምትገኝበት አጠቃላይ እውነታ ሳስብ፤ በተሻለ መልኩ ሊገልፀው የሚችል ሆኖ የተሰማኝን አንድ የገጠሪቱ ኢትዮጵያ ህዝቦች ቀልድና ቁም ነገር ነግሬያችሁ ልብቃ።

ነገሩ እንዲህ ነው፤ አንዲት መላው ቤተሰቦቿን በሞት ስላጣች ሐዘን ክፉኛ የጎዳት ኢትዮጵያዊት ሴት በሰሜን ሸዋ አካባቢ ትኖር ነበር አሉ። እናም የፋሽስት ጣሊያን ወራሪ ሰራዊት ሀገራችንን ተቆጣጥሮ

ከቆየባቸው አምስት ዓመታት ውስጥ አንደኛው ዓመት፤ ኢትዮጵያውያን አርበኞችን ለመደምሰስ ወደ አካባቢው የዘመቱ የግራዚያኒ ወታደሮች፤ ሴትዮዋ ቤተሰቦቿን የቀረበችበትን የማሪያም ቤተክርስቲያን ደብር የአርበኞቹ መደበቂያ ሆኗል ብለው ከማመናቸው የተነሳ እሳት ይለቁበታል። ይህን ዕንግዳ ክስተት ስትመለከት ጊዜ ምናልባትም እርምጃውን ፍትሐዊ አድርጋ ሳትወስደው ያልቀረችው የሐበሻ ሴትም ሌባ ጣቷን ሽቅብ ወደ ሰማይ በመቀሰር እንዲህ አለች ይባላል ...

"አንተ እዚያ ላይ ሆነህ፤ ስትቀልድ በሰው

እናትህ ነደደች፤ ሐዘኑን ቅመሰው...!"

ስትል ፈጣሪን ለመገደደር እንደሞከረች ነው አፋዊ ተረኩ የሚያስረዳው። ታዲያ አሜሪካስ የመከራ ቀምበር በራሷ ላይ ሲወድቅባት እንኳን የሸከሙ ክብደት ሊሰማትና ረጃጅም እጆቿን በሌሎች ሀገራት ህዝቦች የውስጥ ጉዳይ ከማስገባት መታቀብ እንዳለባት ልትረዳ አይገባምን? እንደኔ እንደኔ ከሆነ ግን ለዚያች አገር ህዝብና መንግስት የሚበጀው ዘላቂ መፍትሔ በሌሎች የውስጥ ጉዳይ እየገቡ ለመፈትፈት ሲሞክሩ የሚስተዋሉበትን ማን አለብኝነት ማቆም ነው ባይ ነኝ። ስለዚህም ልቦና ይሰጣቸው ዘንድ እየተመኘሁ ለዛሬ እዚህ ላይ አበቃሁለ። ***መዓሰላማት!***